በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 212528

ሐምሌ 27 ቀን 2014 ዓ.ም

ዳኞች፡- እትመት አሠፋ

ዐሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሣዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡- በጉምሩክ ኮሚሽን የአዲስአበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ተጠሪ፡- እነ ግዛቸው አበበ / 26 ሰዎች

1. ግዛቸው አበበ
2. ኩምሳ አብዲሳ
3. ደረጀ ቦጋለ
4. ደረጃ ለገሰ
5. ኤልያስ ግርማ
6. አንዷለም አሰፋ
7. ይሁንልኝ ታረቀኝ
8. አሰግድ መንግስቱ
9. ፍቅረማርያም እሸቱ
10. ካሳዬ ምትኩ
11. ብሩክ ወርቅነህ
12. ሁሴን ጀማል
13. ቦንሲቱ ሞላድ
14. መባረክ አባጀማል
15. እስጢፋኖስ ይርዳው
16. ምትኩ ጨምሳ
17. ኢሳያስ አስናቀ
18. አሸናፊ ኩምሳ
19. መሀመድ አህመድ
20. ሐብታሙ ስርጋዊ
21. ሀይሉ ሙለታ
22. መሳይ ታሪኩ
23. ትዕግስት አሸናፊ
24. ኤልያስ ጀማል
25. ገረመ ጪምሳ
26. ዋለልኝ ታሪኩ

መዝገቡ ለምርመራ የተቀጠረ ነው። በመሆኑም መርምረን ተከታዩን ፍርድ ሰጥተናል።

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ፍርድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ነሐሴ 06 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 285516 ታሕሳስ 23 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 190739 ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት አቤቱታ በማቅረባቸው ነው።

ጉዳዩ የቅድሚያ መብት ክፍያን አስመልክቶ የቀረበ አቤቱታን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ነው። በሥር ፍ/ቤት በተደረገው ክርክር አብዲ አባብያ ሸርክና ማሕበር የፍርድ ባለመብት፤ ዩቲሲ ኤልሳሜክስ ኢኮ አስፋልት ኢትዮጲያ 35 ፕሮጀክት የፍርድ ባለዕዳ፤ የአሁን ተጠሪዎች 1ኛ ጣልቃገቦች፤ የአሁን አመልካች ደግሞ 2ኛ ጣልቃገብ በመሆን ተከራክረዋል።

የአሁን ተጠሪዎች ለስር ፍርድ ቤት ባቀረቡት አቤቱታ በስር የፍርድ ባለዕዳው ላይ በአዋጅ ቁጥር 377/1996 መሠረት ክስ አቅርበው ብር 5,483,821 / አምስት ሚልዬን አራት መቶ ሰማንያ ሶስት ሺህ ስምንት መቶ ሀያ አንድ / እንዲከፈላቸው የተወሰነላቸው መሆኑን እና የቅድሚያ የክፍያ መብት ያላቸው መሆኑን በመግለጽ የፍርድ ባለዕዳ ንብረት ተሸጦ ከሚገኘው ገንዘብ ላይ በቅድሚያ እንዲከፈላቸው ይታዘዝላቸው ዘንድ ዳኝነት ጠይቀዋል።

የአሁን አመልካች በበኩሉ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39/1 መሠረት የቅድሚያ መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ ከፍርድ ባለዕዳ ላይ የሚፈለገውን ቀረጥ እና ዕዳ ብር 98,474,858.17 / ዘጠና ስምንት ሚልዬን አራት መቶ ሰባ አራት ሺህ ስምንት መቶ ሀምሳ ስምንት ብር ከአስራ ሰባት ሳንቲም / ማስከፈል ይችል ዘንድ የቅድሚያ መብት እንዲጠበቅለት ጠይቋል።

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የፍርድ ባለመብቱ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ካደረገ በኋላ የገቢዎች እና ጉመሩክ ባለስልጣን የታክስ ክፍያን አስመልክቶ ታክስ በሚከፍል ሰው ንብረት ላይ የቅድሚያ መብት እንዳለው በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39/1 ላይ የተደነገገ ቢሆንም በኋላ በወጣው የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀጽ 168 ለሰራተኛ የሚከፈል ክፍያ ከማንኛውም ክፍያ በፊት ቅድሚያ እንዳለው ተደንግጓል፤ ስለሆነም በፍርድ ባለዕዳው ሁለት ተሸከራካሪዎች ላይ የተፈጸመው የጨረታ ሽያጭ ተሰርዞ የቅድሚያ ክፍያ መብት ይጠበቅልኝ በማለት የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት የለውም በማለት ተሸከርካሪዎቹ ተሸጠው የተገኘው ብር 5,320,000 / አምስት ሚልዬን ሶስት መቶ ሀያ ሺህ / ላይ ተጠሪዎች የቅድሚያ መብት አላቸው በማለት ወስኗል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል። ይግባኙ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ግራቀኙን ካከራከረ በኋላ አመልካች የፍርድ ባለዕዳው

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

አልከፈለኝም የሚላቸው የቀረጥ እና ታክስ አይነቶች ምንድናቸው የሚለውን ከእያንዳንዳቸው የገንዘብ መጠን ጋር ዘርዝሮ እንዲያቀርብ በይግባኝ ክርክሩ ደረጃ እድል ቢሰጠውም ከቀረጥ እና ታክስ ነጻ እና በጊዜያዊነት ወደ አገር በገቡ ዕቃዎች ላይ ያልተከፈለ ቀረጥ እና ታክስ በማለት በጅምላ ከመግለጽ ውጪ ዘርዝሮ አላቀረበም፤ በአዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39 በመርህ ደረጃ የሰራተኛ ደመወዝ ክፍያ ከቀረጥ እና ታክስ ክፍያ በቅድሚያ ሊከፈል እንደሚገባ ተደንግጓል፤ በልዩ ሁኔታ ደግሞ ከታክስ ከፋዩ ተቀጣሪዎች ደመወዝ ቅድሚያ ሊከፈሉ የሚገባቸው የታክስ ዓይነቶች በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 33(1)(ሀ) የተዘረዘሩ ሲሆን አመልካችም አልተከፈለኝም የሚላቸው የታክስ ዓይነቶች እነዚሁ ስለመሆናቸዉ ዘርዝሮ ያላቀረበ እና ያላስረዳ በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ለተጠሪዎች የቅድሚያ ክፍያ መብት በመጠበቅ የሰጠው ውሳኔ ተገቢ ነው ሲል አጽንቶታል።

አመልካች ነሐሴ 06 ቀን 2013 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ተፈጽሞበታል በሚል የቀረበ ሲሆን ይዘቱም፡- የፍርድ ባለዕዳው ተሸከራካሪዎች ለመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት ስራ ሲባል በጊዜያዊነት ቀረጥና ታክስ ሳይከፈልባቸው ወደ ሐገር ውስጥ የገቡ ናቸው፤ የፍርድ ባለዕዳው ስራውን አቋርጦ ቀረጥና ታክሱን ሳይከፍል ከሐገር ወጥቷል፤ አመልካች በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39 መሠረት ከማናኛውም ክፍያ በፊት የቀረጥ እና ታክስን ለማስከፈል የቅድሚያ መብት አለው፤ ስለሆነም ይህ ታልፎ የአመልካችን የቀደምትነት መብት ውድቅ በማድረግ በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት የተፈጸመበት በመሆኑ በሰበር ታይቶ ሊታረም ይገባል የሚል ነው።

የሰበር አጣሪው ችሎት የአመልካችን የሰበር አቤቱታ መርምሮ የሠራተኞች መብት ከመንግስት ቀረጥ እና ታክስ ቅድሚያ መብት አለው በማለት የሥር ፍርድ ቤት የወሰነበትን አግባብ ከአዋጅ ቁጥር 1156/11 አንቀጽ 168 እና አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 33/1(ሀ)፤ 39 ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ ለመመርመር የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪ መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል።

ተጠሪዎች በአዲስዘመን ጋዜጣ ጥሪ ተደርጎላቸው ስላልቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል።

የግራቀኙ ክርክር እና በየደረጃው ባሉ ፍርድ ቤቶች የተሰጠው ውሳኔ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ነው። ይህ ችሎትም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገባዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራቀኙ ክርክር፤ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል።

ከፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 33 እና 39 ድንጋጌዎች በግልጽ መገንዘብ እንደሚቻለው የሰራተኛ ደመወዝ ክፍያ ከቀረጥ እና ታክስ ክፍያ በፊት በቅድሚያ ሊከፈል እንደሚገባ በልዩ ሁኔታ ደግሞ ከተከፋይ ሒሳብ ላይ ተቀንሶ በሚከፈል ታክስ፤ በተጨማሪ እሴት ታክስ፤ በተርን ኦቨር ታክስ

ወይም በኤክሳይስ ታክስ ከሠራተኞች ደመወዝ ቅድሚያ ሊከፈሉ የሚገባቸው የታክስ ዓይነቶች መሆናቸውን ነው።

በያዝነው ጉዳይ አመልካች በደፋነው ከፍርድ ባለዕዳው ላይ የምፈልገው የቀረጥ እና ታክስ ክፍያ ስላለ በፌዴራል ታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 39 መሠረት የቅድሚያ ክፍያ መብት ሊጠበቅልኝ ይገባል በማለት ከሚከራከር በቀር በእርግጥም ከፍርድ ባለዕዳው ላይ የሚፈልገው ክፍያ በአዋጁ አንቀጽ 33(1) ላይ የተዘረዘሩትን ክፍያዎች መሆናቸውን በሚያሳይ መልኩ ዘርዝሮ እንዳላቀረበ የስር ይግባኝ ሰሚው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰጠው ውሳኔ ላይ በግለጽ ተመልክቷል። ስለሆነም ይህንኑ መሠረት በማድረግ የስር ፍርድ ቤቶች የአመልካችን የቅድሚያ ክፍያ መብት ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ለተጠሪዎች የቅድሚያ ክፍያ መብት በመፍቀድ የሰጡት ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የተፈጸመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት አላገኘንበትም። በዚህም ምክንያት ተከታዩን ውሳኔ ሰጥተናል።

ውሳኔ

1. በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት በመ.ቁ 285516 ታሕሳስ 23 ቀን 2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ ይህንኑ ውሳኔ በማጽናት የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ቸችሎት በመ.ቁ 190739 ግንቦት 30 ቀን 2013 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1 መሠረት ጸንቷል።
2. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪ ግራቀኙ የየራሣቸውን ይቻሉ።
3. ነሐሴ 11 ቀን 2013 ዓ.ም በመዝገቡ የተሰጠው የዕግድ ትዕዛዝ ተነስቷል። ይጻፍ
   - መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል። ይመለስ

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለማንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም